# ለአፍሪካ ህብረት መስራቾች

እኛ አናውቃችሁም እናንተም አታውቁን
እናንተ እሩህሩሆች ተነሱ አድኑን
በስም በዝናችሁ ዛሪ ያወቅናችሁ
ለአፍሪካ አህጉር መብራት ነበራችሁ
ህዝባችሁ ያነባል ሌት ተቀን ይደማል
ፈጣሪም እረስቷል ያፍሪካን ምስል
እረሀብ ጦርነት ጭራሽ አጥቁሮናል
ከዚህ ለጥቁር ህዝብ ተቆርቁሪ ጠፍቷል

መቃብር ከፍታችሁ ተነሱ አጽናኑን
ደርሰንካችኋል አይዞአችሁ በሉን
የሞታችሁ ሁሉ ኧረ ብድግ በሉ
አፍሪካ ነዷለች ተቃጠለች አሉ
ልጆቿም በረሀብ በባሩድ ተበሉ

የ ኦ.ኤ.ዩ መስራች ዛሬ የታላችሁ
ፍቅር ከተስፋ ጋር የተላበሳችሁ
አፍሪካን አድኗት አንድ ሆኖ ልባችሁ
ለጥቁር ተሟጋች እናንት ነበራችሁ
አፍሪካ አዳራሽ አጥቷል አሉ መላ
በ ተ.መ.ድ መመሪያ አፍሪካ ተብላላ
መንፈሳችሁ ይምጣ በአዳራሹ ይሙላ
ፈረሰ ታሪኩ ቃልኪዳን መሀላ

ሰባዊነት ጠፍቶ ሁሉም ተጨካክኗል
በአፍሪካ አዳራሽ መመካከር ቀርቷል
ሁሉም ተናንቆ መዘላለፍ ሆኗል
ጡንቻ መተያያ ሆኗል አዳራሹ
ያራዊት ስብሰባ ሆኗል ባመሻሹ

በ.ተ.መ.ድ መመሪያ መጓዝ ተጀምሯል
በራስ መተማመን አዳራሹ ረስቷል
የአፍሪካውያን እድል በነጭ ተወስኗል
በንክዋሜንኩሩማ በፓትሪስ ሉሙምባ
ቀ.ኃ.ሥ ሴንጎር በሀቢብ ቡርጊባ
ለአፍሪካ ተሟጋች ፈጥረው ነበር አንባ
ጆሞኬኒያታ ገማል አብድል ናስር
ፊሌክስ ሁፌት ጉዋኜ ያኔ የነበር ፍቅር
ዙሪያውን አጥረውት በአንድነት አጥር
አጥር ማገር ፈርሶ አፍሪካ ፈራርሳ
ያፍሪካውያን ኑሮ ሆኗል በዳሰሳ

ቀስቅስልን አምላክ ይነሱ የሞቱ
እስቲ ተነሱና አፍሪካን መስርቱ

EthioLion.Com

ያአፍሪካ ልጆች በመቅሰፍት ተመቱ
እረሀብ ጦርነት በርክቷል ስደቱ
ከዚህ ከከርታታ ከጥቁር ህዝባችሁ
ከአፓርታይድ ግዛት ነጻ ያወጣችሁ
የአፍሪካን አንድነት የመሰረታችሁ
በአንድነት ተነሱ እስቲ እንያችሁ
አፍሪካ በጎሳ በመንደር ከልኳል
በመሪዎች ጡንቻ አፍሪካ ተረግጧል
የኛነታቸውን ፍጹም ጠርጥረናል
ፈጥሮ የነበረው እምካክም እረሳን
ደጉ ቀን ቅረበን ከፉ ቀን እራቀን

ወንድወሰን ሰብስቤ
COVENTERY

EthioLion.Com